# ቅባት ምንድነው? (24)

## (ከየተለያዩ ክፍሎች የተውጣጣ)

የጥናት ዓላማ፡ ክርስቶስን በማመን የእግዚአብሄር ልጅነትን ያገን ሁላችን ለክህነት የሚያበቃንን የመንፈስ ቅዱስ ቅባት የተቀበልን ስለሆነ ሌላ ለመቀባት የምንጠብቀው ተጨማሪ ቅባት ሊኖር እንደማይገባን አስረግጠን እንድንረዳ ለማድረግ፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹እናንተ ግን ከእርሱ ከቅዱሱ ቅባት አላችሁና ሁላችሁም እውነትን ታውቃላችሁ… እናንተ ግን ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በውስጣችሁ ይኖራልና፡፡›› 1ኛ ዩሐ 2፡20, 27

1. ዘጸ 30፡22-33 በአንድነት ይነበብ፡፡ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስለ ቅባቱ የምታያቸውን ሃሳቦች ሁሉ አንድ በአንድ በመዘርዘር ተናገር፡፡ በክፍሉ ውስጥ በማጠቃለል ሲነገር በቅባቱ የሚቀቡት ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
2. ክፍሉ ዕቃዎቹ የሚቀቡበት ምክንያት ምን ነበረ ይላል? አሮንና ልጆቹስ ስለሚቀቡበት ምክንያት ምን ይነግረናል? ዘጸ 40:15 ስለ ክህነታቸው የጊዜ ገደብ ምን ይነግረናል?
3. 1ኛ ነገ 19፡16ትን ስናነብ ከካህናት ሌላ ይህንን ቅባት እንዲቀቡ ያዘዛቸው ሌሎች ሁለት ዓይነት ሰዎችን እናያለን፡፡ ስለ እነዚህ ሁለት ዓይነት ሰዎች ምንነት ተናገር፡፡
4. 1ኛ ጴጥ 2፡9፣ ራዕ 1፡6ትንና፣ ራዕይ 5፡10ትን ስናነብ ስለአማኝ የሚናገሩት የጋራ የሆነ አንድ  የምታየው ሃሳብ ምንድነው?
5. በዘጸ 30፡30 ላይ ስንመለከት በብሉይ ኪዳን ለክህነት ለሙብቃት የተቀደሰውን ቅባት መቀባት የግድ ነበረ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ለአዲስ ኪዳን አማኞች ለአገልግሎት ብቃት ስለተሰጣቸው ቅባት አስረዳ፡፡ ሉቃ4፡18ትን፣ ሥራ 1፡8ትንና 10፡38ትን መመልከት ይረዳል፡፡
6. 2ኛ ቆሮ 1፡21-22ትን አንብቡት፡፡ ይህ ክፍል ተቀብቷል እያለ የሚናገረውማንን ነው? የተቀባውን ብቻ ሳይሆን ክፍሉ ቅባቱን ስለሰጠውም ይናገራል፡፡ ቅባቱን የቀባው ማን ነው ይላል? 1ኛ ዮሐ2፡20፣27 በዚህ ክፍል ያለውን እውነት የሚያጠናክርልን በምን መንገድ እንደሆነ ተናገር፡፡
7. በብሉይ ኪዳን በተመለከትነውና ቅባትና በአዲስ ኪዳን ቅባት መሃል የሚታዩህን ማናቸውንም ዓይነት ተመሳሳይነቶችም ሆኑ ልዩነቶችን በማነጻጸር ለመናገር ሞክር፡፡
8. በዕብ1፡9 መሰረት ከሌሎች በበለጠ መንገድ ቅባቱ አለበት ማለት ቢያስፈልግ ሊጠቀስ የሚችለው አንድ ሰው ማነው ማለት እንችላለን?
9. በዘመናችን ስለቅባት የምትሰሚቸውን ትምህርቶች ዛሬ ካየናቸው የመጽሀፍ ቅዱስ ክፍሎች ጋራ በማስተያየት የምታስተውሏቸውን ግንዛቤዎች ተወያዩባቸው፡፡ መንፈስ ቅዱስ በውስጥህ  ካለ (ሮሜ8፡9) ተቀብተሃልና ሌላ የምትጠብቀው ቅባት ሊኖር አይገባህም፡፡

በወንድሙ ሃብተወልድ ተዘጋጀ  (253) 653-4707
ethiowengel.com